# የሃይማኖት ነፃነት እና ዜግነት
# (የአክራው ቻርተር)

## መግቢያ

የሃይማኖት መሪዎች በአፍሪካ ስለቤተክርስቲያንና መንግሥት ትስስር ጉዳዮች አበክረው ሊያስቡ ይገባል። ምክንያቱም ችግሩ በአጣዳፊ ሁኔታ እየገዘፈና አሳሳቢ እየሆነ ማህበረሰቦቻቸውንም እያናወጠ ስለሚገኝና፤ የፓለቲካው አለመረጋጋት በሕዝብ ተቋማት ላይ ሊኖር የሚገባውን መተማመን ክፉኛ በመሸርሸሩ ምክንያት ነው። ሙስና እና የሞራል መላሸቅ መተማመንንና ሰላምን ወይም የደህንነት ስሜትን አዳክሞታል ማለት ይቻላል። በቅርቡ በቱኒዝያ፤ በአልጀሪያ፤ በግብፅ እንዲሁም በሊቢያ የሚገኙ ዜጎች ተነስተው የሚያስተዳድራቸው መንግሥታት ላይ ድምፃቸው እንዲሰማ ማድረጋቸው እዲሁም በተለያዩ አህጉሪቷ ለሚገኙ የጨቋኞች ጥቃት ሰለባዎች ለሆኑቱ ሁሉ የተስፋ ጭላንጭል ፈንጥቋል። በጥቅሉ እየተስፋፋ የመጣው የሕዝቦች /የሲቪል ሥርዓት/ መፋለስ በሃይማኖት ተቋማት እና በምእመናን መካከል ክፍፍልና ልዩነቶች እየፈጠረ እንደሰደደ እሳት እየተቀጣጠለ ያለው ችግር የሃይማኖት መሪዎች አፋጣኝ ምላሽ እንዲሰጡ ግድ ብሏቸዋል።

የሃይማኖት ተቋማት በአፍሪካ የዜጎችን ቁሳዊ ኑሮ እና ሁኔታ ለመቀየር የሚያስችል በቂ ሃብትና ንብረት የላቸውም፤ ስለሆነም ሃይማኖታዊ ጥሪያቸውን ቸል በማለት አሊያም በከፋፋይ ፓለቲካ ራሳቸውን በመዝፈቅ፤ ወደጎን በመገፋትም ድምፃቸው ይታፈናል፤ ወይም በተለያዩ መንገዶችና ሰበቦች ድምፃቸው ፈጽሞ አይሰማም።

ብዙ ታዛቢዎች እንዳጤኑት የሃይማኖት መሪዎች ጥቅምን መርጠው በስልጣን ላሉት “የነፍስ አባት” በመሆናቸው ሳቢያ ቤተክርስቲያንን ምግባራዊ ምስክርነት ዝቅጠትና የፓለቲካ ማሳያ መድረክ አድርገዋታል። ይህም ተስፋን እያደበዘዘ እና ግብታዊ ኀይልን አላግባብ መጠቀምን እያበረታታ መልካም አስተዳደርን እያጨለመ ይገኛል። ዘመን አልፎ ዘመን ሲተካም ስልጣንን ያለአግባብ መጠቀም ጭቆናና ጉዳቶች ወደተስፋ መቁረጥና ለውጥ ፍለጋን ሊቀሰቅሳቸው ይችላል።

በተለያዩ አገሮች የብሔራዊ ተቋማት የውድቀት አጥቢያ ነፍስ ያላቸውና የሚሰሩ የሃይማኖት ተቋማት ብቻ ሆነው ሊገኙ ይችላሉ። በመሆኑም የሃይማኖት መሪዎች ለሃይማኖት ተቋማቱ ጽናትና ተጽዕኖ የማምጣት አቅምን፣ የተስፋ ጭላንጭል በተዳከመበት ወቅት ስለተስፋቢስነት እንዲሁም ስለሰላም ፍትህ እና ዕርቅ ጉዳይ ለመናገር ሲፈቅዱ ሃይማኖታዊ ድምፆች በሕዝባዊው መድረክ ላይ ተሰሚነታቸው የጎላ አስተውጽኦ ይኖራቸዋል።

ምርጫው በአንድ በኩል በሃይማኖታዊ ቅባት አምባገነናዊ ኃይል በሌላ በኩል ደግሞ ለግብረገብ ግድ የለሽነት ወይም ለለዘብተኝነት በመልቀቅ ሳይሆን በተስፋ መቁረጥና በተስፋ መካከል ይገኛል። የመንግሥት አስፈላጊነት በተጓዳኝነት ጨቋኝነትም አይቀሬ ነው ማለት ግን ልክ አይደለም። ዲሞክራሲያዊ ከለላ ከተደረገለት አንዱ ከሌላው ጋር ሳይዳበል ሊኖር ይችላል። እንደተለመደው መኖር (ባለህበት እርገጥ) ከሆነ ግን የሚደርሰውን ችግር የሚታገሱት አይሆንም።

የሃይማኖት መሪዎችም ሁል ጊዜ የሚገጥማቸው የመንታ መንገድ ምርጫ ይሄው ነው። ቁጥራቸው በየዕለቱ እየተበራከቱ የሄዱት ዜጎችም ሕይወታቸውንና

አኗኗራቸው በጨቋኝ የፖለቲካ አገዛዞችና ክፉ ባለሥልጣኖች አሉታዊ ተጽዕኖ ሥር የሚኖሩ ተጠቂዎች ራሳቸውን ሃይማኖታዊ አድርገው በሚቆጥሩ ድርብ ዜግነታቸውና አማኝነታቸው ለእግዚአብሔርና ለእነርሱ ቢጤም ለሰው ልጅ መስጠት ያለባቸውን ጠንቅቀው የሚያውቁና ግራ ያልተጋቡ ሰዎች ናቸው። ጉዳዩ የአንዱን ወይም የሌላውን የመምረጥ ነገር አይደለም። የመንግሥት ተጠሪነት ለሕዝቡ ይሁንታ/ስምምነት መሠረት ሊሆን ይገባል ብለው ሲያስቡ የሕጉን የበላይነት ማክበር እንደሚገባም ያምናሉ።

መንግሥት የዜጎቹን ፍፁም መገዛትንና ሎሌነት ለራሱ ህልውና ብቻ ሲል እንዲሁ እግዚአብሔርንና ባልንጀራህን መውደድ የሚለውን ሕግ መከለከል አይገባውም። ብዙ አፍሪካውያን በህዝባዊ ጉዳዮች ንቁ ተሳታፊ ሲሆኑ ጥምር ዜግነታችውን እንደአማኝ ቸል አይሉም። እናት ቤተክርስቲያናቸውና መንግሥታቸው የተለያዩ ተቋማት መሆናቸው እንደተጠበቀ ሆኖ ማለት ነው።

የፓለቲካ ውድቀቱ ገሃዳዊ እውነታ፣ ሃይማኖተኝነቱና የሃይማኖት መሪዎች አዲስ ሃሳብን በማመንጨት የዜግነት መብትን በተመለከተ መተማመን እንዲመለስና የራሳቸውን ፖለቲካዊ እጣ ፈንታ መወሰን እንዲችሉ እና አማኞች ለእግዚአብሔርና ለባልንጀራቸው ያላቸውን ለመስጠት የሚያስችል ማዕቀፍ ሃይማኖት በመሆኑ ሃይማኖትና ፖለቲካ በጣምራነት ይገናኛሉ። ዜጋ እና አማኝ ያው አንድ ግለሰብ ስለሆነ ደግሞም ለአማኝ የዜጋ የፈቃድ ይሁንታ/ ስምምነት (consent) ከአንድ ምንጭ በአስገዳጅ ስምምነት (dictates of conscience) የተቀዱ ናቸው። ሁሉም ዜጎች አማኞች ባይሆኑም ሁሉም አማኞች ግን ዜጎች ናቸው። ጥምር አቋም (dual status) በአማኞች ላይ ድርብ ሃላፊነቶች ማለትም የመንግሥትን ሥርዓትና ሕግ በማክበርና እንዲሁም በህሊና ሕግን ለእግዚአብሔር በመታዘዝ ያደርጋሉ።

እነዚህ ሃሳቦች በጋና የአክራው የሃይማኖት ነፃነት እና ዜግነት ቻርተር መነሻ ዳራ ናቸው። በአክራ በጁላይ 2010(እ.ኤ.አ) *የክርስትናና የእስልምና ግንኙነት በአፍሪካ* በሚል በተደረገ ጥልቅ ስብሰባ የሙስሊም እምነት በማኅበረሰብ ሥርዓት ስላደረገው አስተዋፅኦ እውቅና ሰጥቶአል። በክርስትናም በኩል ስለሃይማኖት ነፃነትና ዜግነት የተሰጠው እውቅና ቢዳብር ክርክሩን አሁን ካለበት ጊዜያዊ ተግዳሮት ያላቅቀዋል። እስላማዊው የማኅበረሰብ ቅርፅ በተቀረው ክርስቲያናዊ አፍሪካ አቻ የለውም። የደቡብ አፍሪካውን አፓርታይድን እንደተለዩ ምሳሌ ካልቆጠርነው በስተቀር። አዲስ ኪዳን ስለሃይማኖታዊ መንግሥት የሚሰጠን ምንም አይነት መሪ ካርታ የለም። የጥንቷ ቤተክርስቲያን እንድትከተለው የተሰጠ እና ሙስሊሞች ሂጅራ የሚሉት አይነት የሙሊሙ ጂሃድ ፊ ሳቢል ሊ-ኢላሂ "በአላህ መንገድ መታገል" የሚሰኘው ፖለቲካዊ አወቃቀርና ህቡዕ እንቅስቃሴ (mobilization) ግን መፅሐፍ ቅዱስ እና የክርስቲያን ትውፊት እጅግ አስፈላጊ የሃይማኖት እና ሕዝባዊ አስተዳደር ሞዴል ይሰጡናል። በተለይም ድርብ ማንነትን (dual identity) በእግዚአብሔር መልክ እና አምሳል እንደተፈጠረ ሰው እና የቄሳር ተገዢ ህዝቦች ማለት ነው። የአክራው ቻርተር ጥምር ቅርስ በእምነትና በጋራ ጥቅም ዙሪያ ጨቋኝነትንና አጉል ፈንጠዝያን ይቃወማል።

## *የአክራው የሃይማኖት ነፃነት እና ቻርተር*

*መንደርደሪያ*

*እኛ የዚህ ሰነድ ፈራሚዎች በጋና አክራ* (*ከፌብርዋሪ* 24 - 26 2011 *እ.ኤ.አ.*) *እንደ አፍሪካ አማኝ ማኅበረሰብ እና አገራት አባላት ስለጥምር ዜግነታችን ለማስመስከር ተሰበሰብን። ስለዚህ ጥምር ዜግነት ጉዳይ ተገናኝተን ለመምከር ስንወስን እነዚህ ኀላፊነቶች በአህጉራችን ከፍተኛ ጫና መኖሩን ታዝበናል። የተለያዩ አብያተክትስቲያናትን እንዲሁም ሃገራትን ወክለን ተገኝተናል፡፡ ለምሳሌ በእርስ በርስ ጦርነት ሃይማኖታዊ ወገኖች ከፓለቲከኞች ባልተሻለ በሆኑባት ኮትዲቯር፤ ሃይማኖታዊ አክራሪዎች በየወገኑ ሠላምን ከሚያደፈርሱባትና የመንግሥት መረጋጋትን ለማምጣት ከሚዳከርባት ናይጀሪያ፤ የተለያዩ እምነት ያሏቸው ፍትህና ሕዝባዊ እርቅ ይመጣል በማለት ተስፋ ከሚያደርጉባት አዲሲቷ ደቡብ ሱዳን ተሰባስበናል። ከሰሜን አፍሪካ ተወክሎ የመጣ በመካከላችን አልነበረም። ነገር ግን በዚያ ለሚኖሩ አፍሪካውያን ወገኖቻችን ክፉውን በመቃወም የተሻለውንና በጎውን ለሁሉ ለማምጣት ለሚታገሉት ልባችንን አንስተን ፀሎታችንን አቅርበናል።*

*በተጨማሪም መንግሥታትና ማህበረሰቦች ጊዜያዊ ተቋማት* (provisional arrangements) *መሆናቸውን ስናበክር በየአገሮቻችን ስንኖር በእምነት የምናዬው "እግዚአብሔር የሠራትንና የፈጠራትን ከተማ" (ዕብራ 11፡9 -10)ነው። እንደክርስቲያንነታችንም ስናስብ ልዩ ሸክም*(*ኀላፊነት*) *ይሰማናል። በበጎ ራእይ ሕያው እግዚአብሔርን ስናመልክ እና የእግዚአብሔርን መንግሥት ስናውጅ ባለሁሉም እምነቶች*/ *ሃይማኖቶች እንደዜጋ አብረው የሚተዳደሩባቸው መንግሥታት የሚገባቸውን ክብር ስንሰጥና ገዢዎቻችንን ስናከብር እግዚአብሔርን ማገልገልና መፍራትን አናቋርጥም*(1*ጴ*ጥ2፡16-17)*። ሁሌም ለጋራ ጥቅም ሁሉም እንደመረዳታቸው ያመኑበትን ሃይማኖት የመከተል ነፃነት*(*ገላ* 5፡13)፤ *መንግሥታት ሰላምንና መልካም አስተዳደርን ለማስፈን የሚጣጣሩበትን ሁሉም የዓለም ታላላቅ ሃይማኖቶች ያስተምሩታል ይሰብኩታልም። መንግሥት ዜጎቹ በነፃነት የመኖር መብታቸውን ሲያረጋግጥና ለሕዝቦቹ ተጠሪነቱንና ተጠያቂነቱን ተግባራዊ ሲያደርግ እውቅና ይሰጣል።*

## መግቢያ

### እምነት፣ ነፃነት እና አገልግሎት

እንደማኅበረሰብ ለመኖር መፈጠራችንን እናስታውቃለን። ይህም መብትና ግዴታን የሚያካትት ሲሆን እንደማኅበረሰብ ሕይወት ቀጣይ ግብአቶችን በመለኮታዊ ሉዐላዊነት ችሮታ እንደ እምነት ማኅበረሰብ አባላት እንኖራለን፣ በአንድ መንግሥት ሥር እንዳሉ ዜጋዎች ግዴታዎቻችንን እንወጣለን (1ጴጥ 2፡13-14)።

ተያያዥነት ያላቸውን ጥምር የዜግነት ሃላፊነቶቻችንን ስናነሣ የቤተሰብ አስተዳደግና ማኅበረሰብ ለሌሎች ግንኙነቶቻችን የሞራል መሠረቶቻችን መሆናቸውን ልናስብ ይገባል። በየመልካቸው መለኮታዊ ሉዐላዊነት እና አገራዊ ሉዐላዊነት ሁለቱም አንዳቸው ሌላቸውን ሳያስወግዱ የእኛን መሰጠት ይሻሉና።

እንዲያውም የሃይማኖታዊው ማኅበረሰብ አባላት መሆናችን የዜግነት ግዴታችንን ሚና ለመወጣት ደጋፊና ተጨማሪ አቅም ይሰጠናል። ጥምር ዜግነታችን የአማኝነትና የዜግነት ጣምራ ሚናዎቻችንን ተደጋጋፊነትን ሲያሳውቅ፣ ነፃነት ደግሞ ሁለቱን የሚያገናኝ ድልድይ ነው። መሪዎቻችንንና ሌሎች ሠዎችን ሁሉ ስናከብር እግዚአሔርን ማገለገልና መፍራትን እንዳናቋርጥ መጽሐፍ ቅዱስ ያዘናል/ያበረታታናል (1ጴጥ 2፡16-17)።

የሃይማኖት ነፃነት የሚፈልቀው ከአማኙ ሕሊና ሲሆን በአገራዊ መንግሥት አንፃር ደግሞ ነፃነት ከዜጎች የፈቃድ ኑዛዜና ይሁንታ ወይም ስምምነት(will and consent) ይመነጫል። ሃይማኖታዊ ነፃነት ከዜግነትና ከመንግሥት አስተዳደር የተነጠለ አይደለም። የታዘዝነውም በነፃነታችን ተጠቅመን አንዳችን ሌላውን እንድናገለግልበት ነውና(ገላ5፡13)።

### ለማመን ተፈጠርን

ስለማንነታችንና ስለተፈጠርንበት ዓላማ ስናስብ ፈጣሪንም እናስባለን። እንደ ሰብአዊነታችን ማህበረሰባዊነታችን፣ የነፃነቶቻችን የግዴታዎቻችንና የሕይወት ምንጫችን እርሱ ነውና። ሃላፊነቶቻችንና መብቶቻችን የሚመነጨው እግዚአብሔር ለበረከት ያዘጋጀልንን ከማወቅ ነው (መዝ 8፡6-8)።

- ወላጆቻችን እንደሕይወት እትብት ተንከባክበው አጽንተውናል
- ዝምድና /ዘመዳማችነት/ ቀርፆናል መስርቶናል።
- የአፍ መፍቻ ቋንቋችዎቻችን ራሳችንና ግንኙነቶቻችንን ተገንዝበን ማንነታችንን እንድናውቅና እንድንገልጥ ቃላቶችን አበርክተውልናል
- ማህበረሰቦቻችን ለወዳጅነቶቻችን ቅርፅ ሰጥተው ጠብቀውልናል።
- ደግሞም እርስበርሳችንን ያስተሳስሩን ሠፊ ግንኙነቶቻችን ከሁለትዮሽ መብቶችና ኀላፊነቶች ጋር ነው።

### ሃይማኖት፣ አገር እና ማኅበረሰብ

እንደ ግለሰብ የቤተሰብ አባልነት ከሌሎችና በሁሉ ሥፍራ ከሚኖሩ ሠዎች ጋር ያለን አጋርነት ተመሳሳይ ስለመሆኑና በግንኙነቶቻችንና በሃላፊነቶቻችን ለመጐልመስ መንደርደሪያ መሆኑን እንማራለን። ይህን ስለራሳችን ያለንን የጋራ እውቀት ይዘን ወደሰፊው ማኅበረሰብ ስንመጣ የቤተሰብና የቤተዘመድ አባልነት

ጥቅሞችና ኃላፊነቶችን እንድንጋራ ያበቃናል። እናም ለመንግሥት ሕጐችና ሥርዓቶች ለጋራ ጥበቃችንና ደህንነታችን ሲባል እንድንገዛ መጽሐፍ ቅዱስ አንዱ ሌላውን እንድንንከባከብ ሲያዘን ይህ ቤተክርስቲያን፣ ማኅበረሰብና መንግሥትን ያስተሳስራል(1 ቆሮ 12፡25-26) ።

እንደ ሃይማኖታውያን ግለሰቦች ፈጣሪን ሳንዘነጋ በነፃነትና በገዛ ፈቃዳችን እርሱን ስናመልክ እንደ ዜጋ ደግሞ የምንጋራቸው ኀላፊነቶች አሉን። መታዘዝ ያለብን የሞራል ግዴታዎቻችን ለመንግሥታዊ ተቋማት መሠረት ሆነው ሕይወትና ንብረት የሚከበርበት፣ እኩይ የሚገታበት፤ አጥፊ የሚቀጣበት እና ፍትህ የሚታይበት ሲሆን በግለሰቦች ጥረት መልካምነትና ልማት ይጎለምስበታል(ምሳ8፡15-17፤ መዝ 128፡2)።

በነፃነትና በጋራ ይሁንታ ወይም በወል ስምምነት የተመሠረተ መንግሥት በጐነት እንዲያብብ ከማመቻቸት ያለፈ ድርሻ የለውም። ሌሎች ነገሮች የሚያስፈልጉት ለሞራል እድገትና እሴቶችን ለማፍራት ሲባል ነው (ገላ 5፡22-23 ፤ ኤፌ 5፡9)።

ለዚህ በጐ ዓላማ አማኞች የራሳቸውን ፍላጎትና መሻት በኑሮዬ ይበቃኛል ማለትን፤ በተለይ ከነሱ ያነሰ ኑሮ ላላቸው እንዲያካፍሉ ይጎተጉታሉ። በአርአያነታቸውም ሌላውን "ፍርድን ታደርግ ዘንድ ፥ ከአምላክህም ጋር በትሕትና ትሄድ ዘንድ አይደለምን?"(ሚክ 6፡8) እያሉ ይዘክራሉ። በእርግጥ የነፃነትን በረከት እንድንጐናፀፍ የተቋቋመ መንግሥት ሊፀና የሚችለው ለሕጉ የበላይነት፣ ለእሴቶች በፍትሐዊነት፤ በእኩልነት፤ በምህረትና በሚዛናዊነት ተጠያቂ ሲሆን ብቻ ነው።

## ጥምር ዜግነትና ርስት/ቅርስ/

የጥምር ዜግነት ግዴታዎቻችን የውል ግዴታዎቻችንና ልዩ ልዩ ጥቅሞቻችን የሚከተሉትን ያካትታል፤

- የቤተሰብና የቤተዘመድ ሁለትዮሽ ማለት የሰጥቶ መቀበል ግንኙነትን የሞራል ብቃት በጉልህ በሚታይበት የዜጋዎቻችን እኩልነት እንደመስታወት ሆኖ ዜግነትና ነፃነት ለሕጉ የበላይነት (rule of law) የሚገዙበትን ያንጸባርቃል (ዕብራ13፡17) ።

- መንግሥታት ተፈጥረው የሚኖሩት በእኛ ፈቃድ ነው። ይህም የሕዝብ መረጋጋትና ሰላማዊ ኑሮ ፍላጐት ለማሟላት ሲባል፤ አማኞችም መንግሥትንና መሪዎችን በፀሎት የመደገፍ ሞራላዊ ግዴታ አለባቸው ብለን እናምናለን። ለመንግሥት መጸለይም የፖለቲካ መመቻቸት ሳይሆን የሞራል ግዴታ ነው(1ጢሞ 2፡ 1-2)።

- ዜግነት በራሱ ሞራላዊ ሰብዕናችንን ሙሉ በሙሉ አይገልጸውም። ምክንያቱም መንግሥት የቤተክርስቲያን ማለትም የሰው ልጅ ክብር ነፃነትና ደኅንነት ማማ የሆነችው ምትክ ሊሆን አይችልምና።

- ጥምር ዜግነታችን የጥምር ውርሳችን /ቅርሳችንን/ ውስብስብነት ሲያመላክት በሕግ ከለላ የሆነው የጋራ ደኅንነታችን ለሁሉ ፈጣሪ መገዛት መሆኑን ያመላክተናል።

- እንደሰብዐዊነታችን ፈጣሪ የሞራላዊ ትምህርት ማለትም የሕይወት ስጦታ፣ የመኖራችን ዓላማ እና የሕያው ነፍስን ክቡርነትና መዳረሻ እርሱ መሆኑን እናሳውቃለን።

- ዜግነታችን በፍላጎቶቻችንና በመሻቶቻችን ላይ የተመሠረተ ሲሆን እንደአማኝ ያለን አቋማችን ደግሞ ከፍጥረታችንና ከአፈጣጠራችን እንደሞራላዊ ሰብአውያን ባሕርይና ክቡርነት የተሰጠን ነው።

- በሞራላዊነት ክታብ(ገመድ) የታሰረ የዜግነት እሳቤ መነሻው ከፈጣሪ ጋር ባለን ሞራላዊ ቅርበት ሲሆን እኛ የሆነውንና የሆንንበት ምክንያት የእግዚአብሔርን መልክ እና አምሳል ስለታደልን ነው።

- ጥምር ውርሶቻንን /ቅርሶቻችንን/ ስናውጅ ሁለቱ ማለትም ፖለቲካዊ ሉዓላዊነት ለምድራዊ ገዥዎችና መለኮታዊ ሉዓላዊነት ለእግዚአብሔርና ለአገልጋዬቹ የተመደበ ነው።

- የዜግነት የውል ግዴታዎች ሲጣሱ የአማኙን ኅሊናና የእግዚአብሔርን ሕግጋት ይጋፋሉ ብለን እናምናለን። ደግሞም የሕሊና ሕግ ሲጣስ መዘዙ መንግሥትና ኅብረተሰቡ ላይ በእኩይ ተጽዕኖ ይንፀባረቃል። የሃይማኖት ነፃነት ሲካድ ዲሞክራሲያዊ መንግሥት ይዳከማል የሕዝቡም ሰላም ይደፈርሳል።

## የነፃነት ሥሯና ቅርንጫፎቿ

ስለግለሰብ ነጻ አስተሳሰብ (individual conscience) እና የጋራ ጥቅም የሚከተሉትን ነጥቦች እናጸናለን።

- ነፃነት (liberty) እግዚአብሔርን የማወቅና የማምለክ ዋነኛ መገለጫው ሲሆን እኛንም ሞራላዊና ለማኅበረሰቡ ብቁ ያደረገን መሠረታችን ነው፡፡

- የትኛውን ሃይማኖትና አምልኮተ እግዚአብሔርን መከተል በነፃነትና በግልጽ መምረጥ መሠረታዊ ሰብዓዊ መብት (fundamental right) ነው።

- በሃይማኖትና በፖለቲካ ጐራ እንዲሁም በግል ምርጫ ሳቢያ አላግባብ ኀይልን መጠቀምንና አፈናን እንቃወማለን።

- ሁሉም ዜጐች ወንዶችም ሆኑ ሴቶች ከሕግ በታች እኩል መሆናቸውን እናምናለን።

- ወላጆች ልጆቻቸውን የማሳደግና የመምራት መብት አላቸው።

- እግዚአብሔርንና ሰውን መውደድ ምንጩ ሆኖ ሕብረተሰቡ የሚያጎናፅፋቸው መልካም መብቶች civic virtue ማለትም ወላጆች የሌላቸውን፣ ባል ወይም ሚስት የሞተባቸውን፣ የተገፉትንና ስደተኞችን ለመንከባከብ እንዲሁም ቤተክርስቲያንን መንግሥትንና ኅብረተሰቡን ለማገልገል መሠረቱ ነው።

- አናሳዎችም ሆኑ ብዙኃኖች አንዱ በሌላው ላይ በኅሊናዊ ፍርድ in matters of conscience (1ቆሮ 6፡1-6) ፈላጭ ቆራጭነትን እናወግዛለን። በአንድነት እንዲህ ዓይነቱን ኀይልን ያላግባብ መጠቀምንና ጉጠኝነትን እንቃወማለን።

- እንደዜጎችና እንደአማኞች ሃይማኖት ከፈጣሪያችን ጋር ያለ ጉዳይ ቢሆንም ይህ ኀላፊነታችን ደግሞ ጭከናና ግፍ የተሞላውን ኀይል አጠቃቀምን እንድንቃወም ግዴታ አለብን። ሁሉም ዜጎች በኅሊና ሕግ እየተመሩ ሙሉ ሃይማኖትን የማከናወን ነፃነት አላቸው (ዮሐ 4፡24)። መንግሥት በመውደድ ወይም በመጥላት ብቻ ተነሳስቶ ሃይማኖትን በማንም ላይ መጫንም ሆነ መከልከል አይገባውም።

- በእግዚአብሔር ያለን አንድነታችን ሲባረክ የሚፀናው በብዛታችን (diversity) ነው። ሁላችንም በአጋርነት እንደሰብዐዊነታችን በጐሣ በብሔር በእምነት አቋም ወይም በሕብረት አጋርነት አንድ ባንሆንም አንዳችን በሌላችን ደስታና መከራ ተሳስረናል፤ ያለንበት ሁኔታና አኳኋን ጉልህ ልዩነቶችቻችን እንደተጠበቁ ሆኖ ማለት ነው (የሐዋ 17፡24-28)።

- የሃይማኖት ነፃነት እንደሰበብ ሆኖ የመከፋፈያ፣ የመነጣጠያና የመጠቀሚያ መሣሪያ መሆን የለበትም። ነገር ግን አማኙንና ዜጋውን ለተመሳሳይ ግብ በመቻቻል፣ በምግባረ ሠናይ ችሮታ እና እርስ በርስ በመከባበር ለመጋበዝ እንጂ (1ቆሮ 3፡10፣7፡21-24፤ 1ጴጥ 3፡8-9)። የበጐነት መንፈስ ማኅበረሰቡ የሚያጎናፅፋቸው መብቶች ወደ ጽድቅ ሊመራ ይችላል። ስለዚህም ተጠሪነታችንም ለፈጣሪያችንና ለሌሎች ሰዎች ሁሉ ነውና (ፊልጵ 1፡9-11)።

## ዓለማዊ እና መንፈሳዊ

ሁለቱም ዓለማት ተፈጥሮአዊው እና መንፈሳዊው የእኛ ናቸው (ሮሜ 12፡1-2)። እግዚአብሔርንና ባልንጀራን የመውደድ ሞራላዊ ግዴታ የጋራ መሠረት ናቸውና። ለመንግሥት የተሰጠው ዓለማዊ ሥልጣን የእኛ የአማኞቹ ድጋፍና ጸሎትን ያሻዋል። በዚህ ምድራዊ የመናኝነት ኑሮ ወደወዲያኛው የእግዚአብሔር ከተማ የመናኝነት ጉዞአችን (ዕብራ 13፡14) ለእግዚአብሔር መታዘዛችን ሌሎችን በማገልገል በሕዝቡ ዘንድ መብቶችን ለማጐናጸፍ ያተጋናል። የሰማያዊው ዓለም ፍጹማዊነት የዚህኛው የምድራዊ ዓለም የመዘጋጀትና የታጋሽነት ልምምድ ያሻዋል (2ጢሞ 2፡22 ኤፌ 4፡3)።

እንደ መርሕ አማኞች በልማት ውጤታማና ታማኝ ዜጎች መሆን ይገባቸዋል። ለግልና ለፓለቲካዊ ጥቅም ብቻ ሳይሆን ሞራል ያለው ዜጋ መሆንና የመልካም አስተዳደር እሴት አርአያ ለመሆን ሲባል እንጂ (ቲቶ 3፡1 1ጴጥ 2፡13-14)።

ይህ ሲባል ግን እንደ ፍጥረታዊያን ውሱንነታችንንና የተፈጥሮ ጸጋዎቻችንን ካልዘነጋን ከምንግራቸው ነገሮች መካከል ገደብ የሌለው ሥልጣን አደገኛነትና ራስን የማምለክ ኀጢአት ይገኙበታል (ኢሳ 13፥11፤ ማቴ 20፥25-28፤ ቆላስ 3፥12፤ 1ጴጥ 5፥ 5-6፤ ያዕ4፥6)። አገራት መላውን የሰው ዘር ቤተሰብን ጥቅም ሲያስጠብቁ እግዚአብሔርንም እያገለገሉ ነው ማለት ይቻላል። ሆኖም የሃይማኖት ነፃነትን ከረገጡት ያንኑ (እግዚአብሔርን የማገልገል) ዓላማ ይቃረናሉ።

## ማጠቃለያ

- እግዚአብሔር በመጋቢነቱ ለጥቅማችን የሰጠንን ሁሉ በተለይም ወላጆች ወደ ሕይወት እንዲያመጡን፣ እንዲንከባከቡንና እንዲጠብቁን መስጠቱን እውቅና እንሰጣለን።

- በማኅበረሰብ ደረጃ ማካፈልንና ቤተሰባዊ ፍቅርን እንዲሁም ለማንነታችን ላስተማሩን ወንድሞቻችንና እህቶቻችን እውቅና እንሰጣለን።

- በቤት፣ በትምህርት ቤትና በጐረቤት ያሉ ዘዬዎች (idioms) በልጅነታችን ልቦናችንን በእውቀትና በመውደድ ስለሞሉልንን እውቅና እንሰጣለን።

- የማህበራዊ ክስተቶች ማለትም የልደትና ሌሎች ሥርዓታዊ በዓላት(rites of passages) ከጋብቻና ከሞት ጋር የተያያዙ ሥርዓቶች እንደ ኢዮቤልዩ ያሉ በዓላት ግንኙነቶች እንደግለሰብና እንደማኅበረስብ አስተሳስረው ይዘውናልና ለነሱም ተገቢውን እውቅና እንሰጣለን።

- በማኅበረሰባዊና ሞራላዊ ባህሪያችን የተቀረጸው ነፃነት ለማኅበራዊ በጎነት (civic righteousness) እና ኀላፊነት ለሚሰማው መንግሥት መሠረቱ ነው ብለን እናምናለን።

- ነፃነት ማህበራዊና ሞራላዊ ባሕርያችንን ቀርጾ ኅብረተሰቡ የሚያገናጽፋቸው መብቶችንና ኀላፊነት የሚሰማው መንግሥት መሠረት መሆኑን እንቀበላለን።

- እግዚአብሔር ለፍጥረት ሁሉ ያለውን የነፃነት የጋራ መሠረትነት እንደአማኝና እንደዜጋ እናሳውቃለን።

- እግዚአብሔር ለፍጥረት ሁሉ ባለው ዓላማ የእኛን ድርሻና ከሰው ልጆች ሁሉ ጋር ያለንን አጋርነት እናጸናለን።

- መንግሥት ከሕግ በታች ለጋራ ሰላማችንና ጥበቃችን እንዲቆም እንጥራለን።

- የቤተሰባዊና ሕዝባዊ እሴቶች (family and civic virtues) የቤትና የማኅበረሰብ መሠረትነት ለልማት ለማህበር (community) እና ለጋራ ጥቅም መብቶች መሆናቸውን እናሳውቃለን።

- ከእግዚአብሔር በታች በጥምር ዜግነታችን ዓለማዊና መንፈሳዊ ጥቅሞቻችን ግዴታዎቻችን በጊዜና በዘለዓለም ሥሩን የሰደደው ማንነታችን ክፍል እንደሆነ እናስታውቃለን።

የሃይማኖት ነፃነት እንደዜግነት ቻርተር ስናውጅ በፍጥነት እየተለዋወጠ ካለው የዓለም መብቶችና ኀላፊነቶች መሰባጠር ጋር መተባበር አለበት በማለት ጭምር ነው።

ሞስት ሬቨረንድ ዶ/ር ሮበርት አቦጋዬ ሜንሳ
የጋና ሜቶዲስት ቤተክርስቲያን የቀደሙ ጳጳስና የኦል አፍሪካ ኮንፍራንስ ኦፍ ቸርችስ (ኤ. ኤ. ሲ. ሲ.) የምዕራብ አፍሪካ ቫይስ ፕሬዝደንት
አክራ፣ ጋና

ሬቨረንድ ዶ/ር ጄ ክዋቤና አሳሞሃ ግያዱ
የድህረ ምረቃ ፕሮግራም ዲን
ቲሪኒቲ ትዮሎጂካል ሴሚናሪ
ሌጎን፣ ጋና

ሬቨረንድ ዶ/ር ጆን አዙማ
ዳይሬክተር ሴንተር ፎር ኢስላሚክ እስተዲስ
ሎንዶን እስኩል ኦፍ ቲዮሎጂ
ሎንዶን፣ ዩኬ

ዶ/ር ጆናታን ጄ ቦንክ
ኤስኪዩቲቭ ዳይሬክተር ኦቨርሲስ ሚኒስትሪስ እስተዲ ሴንተር
ኒው ሃቨን ካናቲከት፣ ዩ ኤስ ኤ

ሬበረንድ ዶ/ር ኤም ዳግላስ ካሬው
ቫይስ ቻንስለር አፍሪካ ኢንተርናሽናል ዩኒቨርሲቲ (የቀድሞው ናይሮቢ ኢቫንጀሊካል ግራዱዌት ስኩል ኦፍ ቲዮሎጂ)
ናይሮቢ፣ ኬንያ

ፕሮፌሰር ጆኤል ኤ ካርፔንተር
ዳይሬክተር ናጌል ኢንስቲትዩት ፎር ዘ ስተዲ ኦፍ ዎርልድ ክርስቲያኒቲ፣
ካለቪን ኮሌጅ
ግራንድ ራፒድስ፣ ሚሺጋን፣ ዩ ኤስ ኤ

ዶ/ር ኩአሲ ኬ ሴሌስቲን
አካዳሚክ ዳይሬክተር ፋትያክ
አቢጃን፣ ኮት ዲቭዋር

ሬቨረንድ አይሳያ ማጆክ ዳኡ
ፕሪንሲፓል ናይሮቢ ፔንቴኮስታል ባይብል ኮሌጅ
ናይሮቢ፣ ኬንያ

ዶ/ር ማይክል ግሌርአፕ
ኤክስኩቲቭ ዳይሬክተር ሴንተር ፎር አርሊ አፍሪካን ክርስቲያኒቲ፣ ኢስተርን ዩኒቨርሲቲ
ሴንት ዴቪስ፣ ፔንሲልቫኒያ፣ ዩ ኤስ ኤ

ዶ/ር ደስታ ሄሊሶ
ዳይሬክተር ኢትዮጵያን ግራዱዌት እስኩል ኦፍ ቲዮሎጂ
አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

ሬቨረንድ ዶ/ር ዴቪድ ኒ አኑም ክፖቢ
ሲኒዬር ሌክቸረር ትሪኒቲ ቲዮሎጂካል ሴሚናሪ
ሌጎን፤ ጋና

ሬቨረንድ ዶ/ር ማቲው ኩካህ
ቪካር ጄነራል ካቶሊክ አርች ዳዮሲስ ኦፍ ካዱና
ካዱና፤ ናይጀሪያ

ሬቨረንድ ዶ/ር ዊሊ ሚካኤል ሊባምቡ
ኮቶሊክ ፋኩልቲስ ኦፍ ኪንሻሳ
ኪንሻሳ፤ ዲሞክራቲክ ሪፐብሊክ ኦፍ ኮንጎ

ሚ/ር ፊሊፕ ኤል ሉንድማን
ፕሬዝደንት ሉንድማን ፋሚሊ ፋውንዴሽን ኢንክ
ፍሬዶኒያ፤ ዊስከንሰን፤ ዩ ኤስ ኤ

ዶ/ር መርሲ አምባ ኦዱዬዬ
ዶይሬክተር ኢንስቲትዩት ኦፍ ዉመን ኢን ሪሊጅን ኤንድ ካልቸር
ትሪኒቲ ቲዮሎጂካል ሴሚናሪ
ሌጎን፤ ጋና

ሞስት ሬቨረንድ ዶ/ር ጆን ኦሎሩንፌሚ ኦናኢዬካን
ሮማን ካቶሊክ አርክቢሾፕ ኦፍ አቡጃ
አቡጃ፤ ናይጀሪያ

ሬቨርንድ ዶ/ር ቤንሃርድት ዬሞ ኩራሼ
ሬክተር አክሮፊ ክሪስታለር ኢንስቲትዩት ኦፍ ቲዮሎጂ ሚሽን ኤንድ ካልቸር
አክሮፖን፤ ጋና

ፕሮፌሰር ላሚን ሳኔህ
ዲ ዊሊስ ጀምስ ፕሮፌሰር ኦፍ ሚሽን ኤንድ ዎርልድ ክርስቲያኒቲ
የል ዲቪኒቲ እስኩል ኦፍ ሂስትሪ የል ኮሌጅ
ኒው ሃቨን፤ ካነቲከት፤ ዩ ኤስ ኤ

ዶ/ር ቲት ቲዬኑ
ዲን ኤንድ ሲኒዬር ቫይስ ፕሬዝደንት ኦፍ ኤዱኬሽን
ቴሪኒቲ ኢቫንጀሊካል ዲቪኒቲ እስኩል
ዲርፊልድ፤ ኢሊኖይስ፤ዩ ኤስ ኤ

ፕሮፌሰር አንድሪው ኤፍ ዋልስ
ፕሮፌሰር ኤሜርተስ ኦፍ ዘ ስተዲ ኦፍ ክርስቲያኒቲ ኢን ነን ዌስተርን ዎርልድ
ዩኒቨርሲቲ ኦፍ አበርዲን ኤንድ ዩኒቨርሲቲ ኦፍ ኤድንብራ፤ እስኮትላንድ